የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ
መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# በኦሮሚያ ክልል በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና በታጣቂዎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ የምርመራ ሪፖርት

የካቲት 2016 ዓ.ም.

www.ehrc.org

## ማውጫ

መግቢያ ........ 1
የሕግ ማዕቀፍ ........ 1
በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ዋና ዋና ግኝቶች ........ 3
ከሕግ/ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች ........ 3
እገታ፣ አስገድዶ መሠወር እና ሌሎች በነዋሪዎች ላይ የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ........ 7
መደምደሚያ ........ 8
ምክረ ሐሳቦች ........ 9

# መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ኅዳር 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ በኦሮሚያ ክልል በሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች እና በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መካከል በተለያዩ ወቅቶች በሚደረጉ ውጊያዎች እና ከውጊያ ዐውድ ውጪ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ሳቢያ በሲቪል ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ዘረፋ፣ የሰዎች እገታ እና መፈናቀል መፍትሔ ለመስጠት የፌዴራል መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ እና ተጨባጭ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት የሚገባው መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። እንዲሁም በሐምሌ 5 ቀን 2015 ዓ.ም. በዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርቱ በክልሉ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ ሆኖ መቀጠሉን በመግለጽ፣ በተለይም የክልሉን ሰላም እና ጸጥታ ማረጋገጥ የፌዴራል እና የክልል መንግሥቱ ቀዳሚ ተግባር እንዲሆን ማሳሰቡ ይታወሳል። መግለጫውን ተከትሎ ኮሚሽኑ በክልሉ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ መከታተሉንና ምርመራ ማድረጉን ቀጥሏል።
2. በዚህም መሠረት በተለይም ከመስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በቄለም ወለጋ፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በሰሜን ሸዋ እና በምሥራቅ ሸዋ ዞኖች ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ የዐይን ምስክሮችን፣ የሕክምና ባለሙያዎችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ አባገዳዎችን እና የመንግሥት አካላትን በአጠቃላይ158 ሰዎችን በተለያየ መንገድ በማነጋገር የተሰባሰቡ ግኝቶችን እና ምክረ ሐሳቦችን በዚህ ሪፖርት አካትቷል።
3. ኢሰመኮ በምርመራው ምክንያታዊ አሳማኝነት (reasonable grounds to believe) የማስረጃ ምዘና ደረጃ ተጠቅሟል።
4. ለዚህ ምርመራ መረጃ እና ማስረጃ በመስጠት የተባበሩ እና አሁንም የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው ተጎጂዎችን፣ ምስክሮችን እና ቤተሰቦቻቸውን ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ኮሚሽኑ በምክንያታዊ አሳማኝነት ያረጋገጣቸው የተወሰኑ ከባድ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች እንዲሁም በሪፖርቱ የተካተቱ የጥሰት ዝርዝሮች ውስጥ ጥሰቶች የተፈጸሙባቸው የአንዳንድ ተጎጂዎች ሰዎች ስም እና ዝርዝር መረጃዎች አልተጠቀሱም።
5. ኢሰመኮ የዚህን የምርመራ ሪፖርት ግኝቶች በተመለከተ ለመንግሥት የጸጥታ አካላት በተለይም በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባሎች መፈጸማቸው የተረጋገጠ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰቶችን በዝርዝር የሚገልጽ እና ምላሽ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን እና ሰላምና ጸጥታ ቢሮ መስከረም 24 ቀን 2016 ዓ.ም. የላከ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ባለማግኘቱ የተቋማቱን ምላሽ በዚህ ሪፖርት ለማካተት አልተቻለም።

# የሕግ ማዕቀፍ

6. ኢትዮጵያ ዋና ዋና ከሚባሉት ዘጠኝ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ሰባቱን ተቀብላ አጽድቃለች። በእነዚህ ስምምነቶች ጥበቃ ያገኙት በርካታ መብቶች የልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ደረጃን ያገኙ ናቸው። ከእነዚህ ስምምነቶች መካከል ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀቻቸው የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ

ቃልኪዳን እና የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር እንዲሁም እንደ ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ያሉ የልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ደረጃን የያዙና ሁሉንም ሀገራት የሚገዙ የሕግ ማዕቀፎች ይገኙበታል። ስምምነቶቹ እና ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግጋቱ በሕይወት የመኖር መብት፣ የማሠቃየት እና ሌሎች ጭካኔ፤ ኢ-ሰብአዊ እና ክብርን የሚያዋርዱ አያያዞች ወይም ቅጣቶች ክልከላ እንዲሁም የአስገድዶ መሰወር ክልከላን እና ሌሎች ሰብአዊ መብቶችም በሰላምም ሆነ በግጭት ወቅት ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋሉ።

7. ከዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አንጻር በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ" በመባል የሚጠራ) መካከል እንዲሁም ከሁለት ዓመታት ወዲህ ደግሞ ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎችን ጨምሮ ሲካሄድ የቆየው ግጭት በመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ታጣቂዎች መካከል የሚካሄድ በመሆኑ፤ በግጭቱ ክብደት (intensity) እና በግጭቱ ተሳታፊዎች አደረጃጀት ደረጃ (organization) መመዘኛዎች መሠረት ዓለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት (non-international armed conflict) መመዘኛዎችን የሚያሟላ ነው። በመሆኑም በግጭቱ ተካፋይ የሆኑ ሁሉም ኃይሎች በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ በተለይም ዓለም አቀፋዊ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶችን የሚመለከተውን የጄኔቫ ስምምነቶች ሁለተኛ ፕሮቶኮል፣ የስምምነቶቹን የጋራ አንቀጽ 3 እና አግባብነት ባላቸው ልማዳዊ ሕግጋት ድንጋጌዎች ተገዢ የመሆን ግዴታ አለባቸው።[1]

8. የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ በጦርነት/በትጥቅ ግጭት ተካፋይ የሆኑ ኃይሎች ሁሉ በጦርነቱ ተሳትፎ የሌላቸውን ሲቪል ሰዎች፣ ተካፋይ መሆን ያቆሙና ትጥቅ የፈቱ የተዋጊ አባላትን ጨምሮ አድሎአዊ ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰብአዊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲያዙ ያስገድዳል፤ የትጥቅ ግጭት በሚካሄድበት ወቅት ተሳታፊዎች በተለይም ተዋጊ ኃይሎችን ከሲቪል ሰዎች የመለየት (distinction)፤ የተመጣጣኝነት (proportionality) እና ጥብቅ አስፈላጊነት (necessity) መርሖዎችን ማክበር እንዳለባቸው ይደነግጋል።[2] በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል በመካሄድ ላይ በሚገኘው ግጭት ተሳታፊ የሆኑት የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎችም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ኃይሎች በሚቆጣጠሯቸው እና በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋትን በማክበር ሲቪል ሰዎች ላይ ጥቃት ከመፈጸም የመቆጠብ ግዴታ አለባቸው።

9. በዓለም አቀፉ የወንጀል ሕግ ማዕቀፍም ከላይ የተመለከቱትን የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ክልከላዎች በመተላለፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሲቪል ሰዎች ላይ ለሚፈጸሙ ጥቃቶች የጦር ወንጀሎች ወይም በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚያቋቁሙ በመሆናቸው በግለሰብ ደረጃ ተጠያቂነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው።

---

[1] Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Protocol II), 8 June 1977, Article 1.

[2] Common Article 3 of the Geneva Conventions, Protocol Additional to the Geneva Convention of 12 August 1949, and relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Protocol II), 8 June 1977, Article 13 and ICRC, Non-international armed conflict, available at https://casebook.icrc.org/law/non-international-armed-conflict accessed on 10/1/24.

10. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) ሕገ መንግሥት በምዕራፍ 3 ሥር ከዘረዘራቸው ሰብአዊ መብቶች በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል እንደሆኑና በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ከሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መርሖዎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም እንዳለባቸው ይደነግጋል። ሕገ መንግሥቱ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ የዘር ማጥፋትን፣ ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎችን፣ የአስገድዶ መሰወር እና ማሰቃየት ወንጀሎች በይርጋ እንደማይታገዱ፤ ይቅርታ እና ምሕረትም ተፈጻሚ እንደማይሆንባቸው ይደነግጋል።
11. በ1996 ዓ.ም. የወጣው ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 270 ሥር ግድያ፣ ማሰቃየት እና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ፣ በኃይል ማፈናቀል፣ ለስለላ ማስገደድ፤ በወጀ /በመያዣነት/ ማገት፣ ማስፈራራትና ማሸበር፣ የጅምላ ቅጣት መጣል፣ የበቀል ድርጊት፣ ንብረት መውረስን እና በድንጋጌው ሥር የተቀመጡ ተመሳሳይ ድርጊቶችን በሰላማዊ ሕዝብ ላይ መፈጸም የጦር ወንጀሎች እንደሆኑ ይደነግጋል።

# በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ዋና ዋና ግኝቶች

## ከሕግ/ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች

12. በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በሲቪል ሰዎች ላይ ለሚደርስ የመብቶች ጥሰት እንደ ዋነኛ ምክንያት የተገለጸው በመንግሥት የጸጥታ አካላት በኩል "ለታጣቂ ቡድኖች መረጃ እና ሎጂስቲክስ ታቀርባላችሁ፣ የቡድኑ አባል ናችሁ" በሚል ምክንያት፤ እንዲሁም በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") በኩልም "ለመንግሥት መረጃ ትሰጣላችሁ፣ የቤተሰብ አባላችሁ በመንግሥት ጸጥታ ኃይል ውስጥ እያገለገለ ነው ወይም ከእኛ ጋር በመሆን አልታገላችሁም/ድጋፍ አላደረጋችሁም" በሚል፣ ምክንያት ሲቪል ሰዎችን ማጥቃት፣ ማንገላታት፣ ማገት እና ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፍሉ ማድረግ ነው። በተመሳሳይ በኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች ከአማራ ክልል ጋር በሚዋሰኑ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች የአካባቢውን ነዋሪዎች በጅምላ "በኦነግ ሸኔነት" በመፈረጅ እና የክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችን በማንሳት በሲቪል ሰዎች ላይ ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ዘረፋ እና ማፈናቀል እንደሚፈጸም ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።
13. ጥቅምት 11 ቀን 2014 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን "ለኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች መድኃኒት ትልካለህ፤ ልጅህ ሸኔን ተቀላቅሏል" በሚል የገርበ ጉራቻ ነዋሪና የሀገር ሽማግሌ ወይም "አባ ከለቻ" የነበሩት አቶ አመንቴ ጋረደው በመከላከያ ሰራዊትና በቀድሞው ኦሮሚያ ልዩ ኃይል አባላት ከመኖሪያ ቤታቸው ተይዘው ገርበ ጉራቻ ከተማ በሚገኘው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ካምፕ ውስጥ ለአንድ ወር ከታሰሩ በኋላ ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. ምሽት ላይ በጥይት ተገድለው አስከሬናቸው ካምፑ አካባቢ መንገድ ላይ ተጥሎ ተገኝቷል።
14. ጥቅምት 20 ቀን 2014 ዓ.ም. የገርበ ጉራቻ ከተማ ነዋሪ የነበሩት ነጋሽ በቀለ፣ አብዲሳ ታደሰ እና አበራ ባሸያ የተባሉ ሦስት ወጣቶች ከገርበ ጉራቻ ከተማ በ 5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኝ በሪቲ ተብሎ በሚጠራ ከተማ ውስጥ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") አባል ናችሁ በሚል በቀድሞው በኦሮሚያ ልዩ ኃይል

አባላት በቁጥጥር ሥር ውለው እስከ ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ በብሪቲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በነበረው በሀገር መከላከያ ሰራዊት ጊዜያዊ ካምፕ/ማቆያ ውስጥ በእሥር እንዲቆዩ ከተደረገ በኋላ ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም. ከነበሩበት ካምፕ ለገ ኮቴ ጉባ ወደ ተባለ ቦታ ተወስደው የተገደሉ ሲሆን፣ አስከሬናቸው ጨፌ በሚባል የከብቶች መዋያ ስፍራ ተጥሎ ተገኝቷል።

15. ሚያዝያ 24 ቀን 2014 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ዞን ወረጃርሶ ወረዳ ነዋሪ የነበሩ መለሳ ስሜ፣ ተስፋዬ ቱሉ፣ ካሳ ታምሩ፣ ደሙ ታዬ፣ ተሰማ አቢ፣ ቦጃ አሰፋ፣ አሸናፊ ቦጃ፣ ማሙሼ ሃብተ፣ ቶሊ ሃብተ፣ ፍቃዱ ደቻስ፣ ሃርቆን አሰፋ፣ ታሪኩ ከተማ፣ ሽለማ ከተማ እና ካሱ ዶቦጭ የተባሉ 14 የአዋሬ ጎልጄ ቀበሌ ነዋሪዎችን የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት አካባቢ በቁጥጥር ሥር በማዋል በመኪና ጭነው ጎሃጽዮን ከተማ ወደሚገኘው የመከላከያ  ሰራዊት ካምፕ ከተወሰዱ በኋላ ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ተገድለው አስከሬናቸው በሰሜን ሸዋ ዞን ወረጃርሶ ወረዳ ልዩ ስሙ አላንቴ ገደል አፋፍ ተብሎ በሚጠራ ቦታ ተጥሎ ተገኝቷል።
16. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት "የተሻለ አስተዳደራዊ መዋቅሮችን ለመፍጠር" በሚል የተወሰኑ ዞኖችን፣ ከተሞችን እና ወረዳዎችን በአዲስ መልክ ለማደራጀት ባሳለፈው ውሳኔ ከባሌ፣ ከቦረና እና ከጉጂ ዞኖች ወረዳዎችን በማጣመር ምሥራቅ ቦረና ዞን እንዲቋቋም ማድረጉን ተከትሎ የካቲት 21 ቀን 2015 ዓ.ም. በጉጂ ዞን፣ ቦሬ ወረዳ የተከሰተ ተቃውሞን ለመበተን በሀገር መከላከያ  ሰራዊት አባላት በተወሰደ ያልተመጣጠነ እርምጃ ሚኤሳ ወደራ፣ ኔንኮ ዋታ እና ወርቁ ዱጎ የተባሉ 3 ሲቪል ሰዎች በጥይት ተመተው ተገድለዋል።
17. ኢሰመኮ ጳጉሜን 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ የአማራ ኢ-መደበኛ ታጣቂዎች በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን፣ አሙሩ ወረዳ በሲቪል ሰዎች ላይ ጥቃት ማድረሳቸውን መግለጹ ይታወቃል። ኢሰመኮ ይህንን ምርመራ ባከናወነበት ወቅት ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች በምሥራቅ ወለጋ ዞን፤ በጊዳ አያና፣ በኪረሙ፣ በሀሮ ሊሙ እና በሳሲጋ ወረዳዎች እንዲሁም በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን፣ በአሙሩና በጃርደጋ ጃርቴ ወረዳዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሲሆን፤ በጊዳ አያና ወረዳ፣ አንዶዴ ዴቾ ቀበሌ፣ በኪረሙ ወረዳ፣ ሀሮ አዲስ ዓለም ቀበሌ፣ እንዲሁም በአሙሩ ወረዳ ሪገቴ፣ ጀቦ ዶበን እና ሰሞ ኢለሙ በተባሉ አካባቢዎች በሲቪል ሰዎች ላይ የተለያየ ዐይነት እና መጠን ያላቸው ተደጋጋሚ ጥቃቶችን መፈጸማቸውን ማወቅ ችሏል። ሰኔ 7 ቀን 2015 ዓ.ም. በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ኪረሙ ወረዳ፣ ወስቲ በተባለ ቦታ ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች በሲቪል ሰዎች ላይ በፈጸሙት ጥቃት በየነ በከሬ፣ ኦልጅራ ቶሌራ፣ አመኑ ሂርኮ፣ ሀይሉ ኢትቻ፣ አሳየ በየነ፣ ቶሌራ ሂርጳ፣ ተመስገን ያያ እና ቢቂላ በቃሉ የተባሉ 8 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን በሌሎች 13 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።
18. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦራ ወረዳ፣ ጀርሜ ቦራ ቀበሌ የአማራ ብሔር ተወላጆች የሆኑ 10 ሲቪል ሰዎችን፣ እንዲሁም ነሐሴ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ፣ መቂ ከተማ 10 ሲቪል ሰዎች ገድለዋል።
19. ሰኔ 19 ቀን 2015 ዓ.ም. ከንጋቱ 11:00 ሰዓት አካባቢ በምዕራብ ሸዋ ዞን፣ አምቦ ወረዳ፣ ጎሮሬቲ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ የነበሩ ሂርጳ ኢዶሳ፣ ደሱ ኢዶሳ፣ ኪሲ ሂርጳ እና ሚልኬሳ ለሊሳ የተባሉ 4 የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ሲቪል ሰዎችን የሀገር መከላከያ  ሰራዊት አባላት "የኦነግ ሸኔ ደጋፊ ናችሁ" በማለት ቤታቸው

በመግባት በጥይት ተኩሰው ገድለዋቸዋል፤ ቀበታ ኢዶሳ እና ደጀኔ ገዳ የተባሉ ሌሎች 2 ሲቪል ሰዎችን ተኩሰው አቁስለዋል፡፡

20. ነሐሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. በምዕራብ ሸዋ ዞን፣ ሊበን ጃዊ ወረዳ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ሲያካሂድ በነበረው የጸጥታ ማስከበር ሥራ “ከኦነግ ሸኔ ጋር ግንኙነት አላቸው’’ በሚል ወደ ባቢቻ ከተማ በመውሰድ ካሰሯቸው 47 የሊበን ጃዊ ሆሮ መራ ቀበሌ ነዋሪ ሲቪል ሰዎች መካከል አቶ ጉዲሳ ነገዎ የተባሉ ሲቪል ሰው በመከላከያ ሰራዊት አባላት በተፈጸመባቸው ከባድ ድብደባ ሕይወታቸው አልፏል፡፡
21. ነሐሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ሳሲጋ ወረዳ በመከላከያ ሰራዊት ሲካሄድ በነበረው የጸጥታ ማስከበር ሥራ በወረዳው ደንጋሲ ጎንጎ ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ ገረመው ተክሉ፣ ሳሙኤል ተመስገን እና ገመቹ ከበደ የተባሉ 3 ሰዎች ‘’የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ተባባሪ ናችሁ’’ በሚል በመከላከያ ሰራዊት አባላት ከተያዙ በኋላ በጥይት ተገድለው አስከሬናቸው መንገድ ላይ ተጥሎ ተገኝቷል፡፡
22. ነሐሴ 4 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት አካባቢ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ በጮቢ ወረዳ፣ በኬ ኦፉ ቀበሌ፣ ጎሮ እና ሽመላ የሚባሉ ቦታዎች የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች ይገኙበታል በማለት የተጠረጠሩ ቦታዎችን ነዋሪዎች እንዲጠቁሙ እና ስፍራው ድረስ እንዲወስዷቸው መጠየቃቸውን ተከትሎ ተባባሪ አልሆኑም ያሏቸውን ዕድሜያቸው ከ11-70 ዓመት የሚገኙ 12 የአንድ ቤተሰብ አባላት ካረዩ አራርሳ እና እናቱ ወ/ሮ አራርሴ፣ ጉርሙ ጅፋራ፣ ተስፋዬ ጅፋራ፣ አበራ ጅፋራ፣ ፊጣ ምልኬሳ፣ ሞጎራ ሚልኬሳ፣ ዱጋሳ አረጋዊ እና ባለቤታቸው ጥሩ ያደሳ፣ ቶለሳ ድርብሳ እና ግርማ በከራ ከሕግ ውጪ ገድለዋል፡፡ ለጊዜው ቁጥራቸው በትክክል ባልታወቀ ሌሎች ሰዎችም ላይ የተለያየ ደረጃ ያለው የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡
23. ነሐሴ 6 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች እና በሀገር መከላከያ ሰራዊት መካከል በነበረው የተኩስ ልውውጥ በወረዳው ሹቢ ገሞ እና ቱቺ ሱመዮ በሚባሉ የገጠር ቀበሌዎች የመከላከያ ሰራዊት አባላት የአካባቢውን ነዋሪዎች “የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎችን ሸሽጋችኋል፤ አሳልፋችሁ ስጡ” በሚል ጥይት በመተኮስ ገልገሉ አብሹ የተባለ ሲቪል ሰው ገድለዋል፤ መሠረት በዶ የተባለችን ሌላ ሲቪል ሰውም አንገቷ አካባቢ ጥይት በመተኮስ የአካል ጉዳት ያደረሱባት ሲሆን፣ ቁጥራቸው በትክክል ባልታወቀ ሌሎች ሰዎች ላይ መጠነኛ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡
24. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ በመግባት ጥቃት ማድረሳቸውን ተከትሎ፤ ነሐሴ 07 ቀን 2015 ዓ.ም. የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ቀበሌዎቹን ከተቆጣጠሩ በኋላ “የተደበቁ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች የሚገኙበትን ለመጠቆም ተባባሪ አልሆኑም” ያሏቸው በወረዳው ቢርቢርሰ ጉዳ ሳቦሌ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑትን ጌታቸው ጉንጆ፣ ዳሌ ጉንጆ እና ቦንሳ መቺ የተባሉትን ወደ ቀበሌው ዋና መንገድ በመውሰድ በጥይት ተኩሰው ገድለዋል፡፡
25. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) ታጣቂዎች በኦሮሚያ ክልል፣ በአርሲ ዞን፣ መርቲ ወረዳ በላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ እና ምሥራቅ ሸዋ ዞን አዋሽ መልካሳ መካከል በሚገኘው እና ልዩ ስሙ ቦፋ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ነሐሴ 7 ቀን 2015 ዓ.ም. ከረፋዱ 5:00 ሰዓት አካባቢ በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ በፈጸሙት ጥቃት 3 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውን እና በሌሎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን

ኢሰመኮ ማወቅ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ ነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. ከአዳማ ከተማ ወደ አርሲ ዞን፣ አቦምሳ ከተማ ይጓዝ የነበረ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከረካሪን በመርቲ ወረዳ ልዩ ስሙ አይፋ ዳገት የተሰኘ ቦታ በማስቆም ታጣቂዎቹ የሚፈልጓቸዉን ሰዎች በስም በመጥራት ካስወረዱ በኋላ 2 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፡፡

26. ነሐሴ 10 ቀን 2015 ዓ.ም. በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን፣ ጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ፣ ሃሮ ዳኢ ቀበሌ ውስጥ በሀገር መከላከያ ሰራዊት እና በኦሮሞ ነጻነት ታጣቂዎች (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) መካከል በነበረው ግጭት “መረጃ አቀባይ ነህ” በሚል በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የተያዘው ኩሉላ ለታ የተባለ ወጣት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ገደማ በጥይት ተገድሎ አስከሬኑ መንገድ ላይ ተጥሏል፡፡
27. ሐምሌ 14-15 ቀን 2015 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ፈንታሌ ወረዳ ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት ሮባ ኑራ የተባለ ሲቪል ሰው በጥይት የተገደለ ሲሆን ቦሩ ጂሎ እና ሻምበል መቶ በተባሉ ሌሎች 2 ሲቪል ሰዎች ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡ በወረዳው ከአማራ ክልል ጋር የይገባኛል ጥያቄ በሚነሳበት ቆርኬ (አውራ ጎዳና) እንዲሁም በቻይና መንገድ፣ ሀሮ ጎጋ እና መሰራ መልካ በተባሉ አካባቢዎች ታጣቂዎቹ ነዋሪዎችን በመሣሪያ በማስፈራራት በተደጋጋሚ ጥቃት በመፈጸም የቀንድ ከብቶችን ዘርፈዋል፡፡
28. ነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ደራ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ላይ በአማራ ኢ-መደበኛ ታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት የጉንዶ መስቀል ከተማ ነዋሪ የነበሩትን አመኑ ተሰማ፣ አቡ ቦጋለ እና አሳን ታዬ፤ እንዲሁም የኢሉ ጎዳ ጨፌ ቀበሌ ነዋሪ የነበሩትን አብዱ በቀለ እና ሙሀመድ ሰይድ፤ የራቾ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑትን ቡርቱቃ ውበቱ እና አቤቱታ ነጋ የተባሉ ሲቪል ሰዎችን በመኖሪያ ቤት፣ በሥራ ቦታ እና በመንገድ ላይ በጥይት የተገደሉ ሲሆን የራቾ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት መርከቡ ውበቱ፣ አለምነሽ አበበ፤ የካቢ ጎሎቻ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ኑራ ቦጋሌ እና ከማል አህመድ የተባሉ ሌሎች ሰዎች ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፤ የግለሰቦች ንብረቶችንም ዘርፈው ወስደዋል፡፡
29. ጳጉሜን 3 ቀን 2015 ዓ.ም. በአምቦ ከተማ ገላሳ ጅፋራ የተባለ ወጣት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ”) “ደጋፊ/አባል ነህ’’ በሚል በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ቤተሰቦቹ ወደሚገኙበት አምቦ ወረዳ፣ ገላና ወዴሳ ቀበሌ ተወስዶ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የሟች ቤተሰቦች ባሉበት በገበያ ቦታ በጥይት ተገድሏል፡፡
30. ጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. በቄለም ወለጋ ዞን፣ አንፍሎ ወረዳ ውስጥ በሀገር መከላከያ ሰራዊት እና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ ኦነግ ሸኔ) ታጣቂዎች መካከል በነበረው ውጊያ፣ በወረዳው ሰዱ ቀበሌ ሁንዴ በንቲ፣ ተመስገን ድና፣ ፍሮ ገጆ እና ዋቅቶላ የተባሉ አራት ወጣቶች በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት በቁጥጥር ሥር ውለው፣ በደንቢ ዶሎ ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ተመስገን ድና ከፖሊስ ጣቢያው 9 ኪሎ ሜትር በሚርቅ ሚኒኮ በተባለ ስፍራ በጥይት ተገድሎ ተገኝቷል፡፡
31. መስከረም 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ጊዳ አያና ወረዳ፣ ቀርሳ ኡርጉገኔ ቀበሌ ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች አቶ ተስፋዬ መርጋን በቤቱ ውስጥ በጥይት ተኩሰው ገድለዋል፡፡ በዚሁ ዕለት ስምሪት ላይ የነበረ አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል አቶ መሀመድ አመዱሌ አረባይ የተባለን የጊዳ ከተማ ነዋሪና ሾፌር በማስገደድ ከጊዳ ከተማ ወደ ኪረሙ ወረዳ እንዲወስደው ካደረገ በኋላ ቡርቃ ሶሩማ የተባለ ስፍራ ሲደርሱ ሹፌሩን በጥይት ተኩሰው ገድለዋል፤ እንዲሁም

በአካባቢው መንገድ ላይ የነበሩ መምህር ነገሮ አብዲሳ እና አቶ እምሩ ቶሌራ የተባሉ 2 ሲቪል ሰዎች ላይ ጥይት በመተኮስ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። መስከረም 4 ቀን 2016 ዓ.ም. በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ከጉቲን ከተማ ወደ ጊዳ አያና ከተማ የሚች መሀመድ አመዱሌ አረባይን ቀብር ለመፈጸም በመኪና ሲጓዙ የነበሩ የሚቹ ቤተሰቦችና ዘመዶችን ጨምሮ 27 የሚሆኑ ሰዎችን የጫነ ተሽከርካሪ ላይ ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች ከጠዋቱ 2፡00-3፡00 ሰዓት ገደማ ድቾ በተባለ ቦታ ላይ ተኩስ በመክፈት መኪናውን ካስቆሙ በኋላ አቶ ቶላ ኑሩ መሀመድ፣ አማኔ ኑሩ እና ቢላደን ጅቦ ኑሩ የተባሉ ሦስት ሰዎችን ከመኪናው አስወርደው በጥይት ገድለዋል ፤ መሀመድ ሼህ ኡመር፣ መሃመድ ፋንታሁን (ባቡ ሀጂ መሀመዴ) እና ፉአድ ጀዋር የተባሉ 3 ሰዎች በተተኮሰባቸው ጥይት ምክንያት በሕክምና ላይ እያሉ መስከረም 05 ቀን 2016 ዓ.ም. ሕይወታቸው አልፏል፤ ሌሎች 3 ሲቪል ሰዎችም በተተኮሰባቸው ጥይት ጭንቅላታቸው፣ ሆዳቸው እና እጃቸው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

32. መስከረም 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ ጊዳ አያና ወረዳ፣ ቀርሳ ቀበሌ ኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች በአንድ ሲቪል ሰው መኖሪያ ቤት ውስጥ በመግባት በፈጸፀሙት ሌላ ተመሳሳይ ጥቃት የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ ኤሊያስ አየለ (አባወራ)፣ ወ/ሮ ኑራ ሰኢዱ (ነፍሰጡር እማወራ) እና መሀመድ ኤልያስ (የ12 ዓመት ሕፃን) ላይ በፈጸሙት ጥቃት ሕይወታቸው ማለፉን ኢሰመኮ ለማወቅ ችሏል ።
33. ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም. ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦሰት ወረዳ፣ ጋሪ ኑራ ቀበሌ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ወ/ሮ ኩለኒ ሀዋስ፣ አቶ ገዳ ጎዳና፣ አቶ ቱፋ ኢደኦ፣ አቶ ቦሩ በቀለ የተባሉ 4 የቀበሌውን ነዋሪዎች "ሸኔን ትደግፋላችሁ" በሚል ይዘው ሶጊዶ በሚባል ቦታ በሚገኘው የመከላከያ ካምፕ ካሰሯቸው በኋላ፤ ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ ከካምፕ በማውጣት በቀበሌው ቢርካ በሚባል ስፍራ 3 በጥይት የተገደሉ ሲሆን፣ ቱፋ ኤደኦ በጥይት ቆስሎ ከባድ አካል ጉዳት ደርሶበታል።

## እገታ፣ አስገድዶ መሠወር እና ሌሎች በነዋሪዎች ላይ የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

34. ጥቅምት 18 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1፡30- 2፡30 ሰዓት ገደማ በኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ የሳሲጋ ወረዳ ውስጥ ዋቅቶሌ ኢምሩ፣ ዘነቡ ዋቅቶሌ፣ ማርታ ነጋሽ፣ መሠረት ምትኩ፣ በልዩ ሽፈራው፣ ሀብተሙ ኡመታ፣ ኪዳኑ ኡመታ፣ ዋቅቶሌ ጉኡዲና፣ በልፋ መኳንንት፣ ድባ ኢራኮ፣ ሲሳይ ኢያሱ፣ አዳሚ ቅናጢ፣ በላይ ረጋሳ፣ ተሰማ ተነኝ፣ ደረጀ ዳባ፣ ሳሙኤል ተመስጌን፣ ጉደታ ኢቢሳ፣ ሚካዔል አበበ፣ ድንቁ ዳባ፣ ዱባለ ቶለሳ፣ ሰልና ተስፋ፣ መርጋ ፍቃዱ እና የአባታቸው ስም ያልተለዩ ተካልኝ፥ ወየሳ እና አማኑዔል የተባሉ በአጠቃላይ 26 የመንግሥት ሲቪል ሠራተኛ ሰዎች በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከነቀምት ከተማ ወደ ሳሲጋ ከተማ እየተጓዙ በነበሩበት ወቅት አዳሚ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎች በኃይል ታግተው ተወስደዋል። ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ እንዳልተለቀቁ እና በሕይወት ስለመኖራቸው ያለመታወቁን ለመረዳት ተችሏል።
35. ሰኔ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦራ ወረዳ፣ በርታ ሰሚ ቀበሌ 2 እናቶች ከ 4 ሕፃናት ጋር፣ እንዲሁም 2 የቀበሌው ነዋሪ ሲቪል ሰዎች በታጣቂ ቡድኑ ታግተው ከተወሰዱ በኃላ፤ ሁለቱ ሴቶችና አራቱ ሕፃናት ሲለቀቁ ሁለቱ

ወንዶች ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ያለመገኘታቸውን ኮሚሽኑ ተዓማኒ መረጃዎችን እየተቀበለ ይገኛል፡፡

36. በሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦራ ወረዳ፣ ከበርታ፣ ሰሚና ጀርሜ ቦራ ቀበሌዎች፣ እንዲሁም በዞኑ በዱግዳ ወረዳ፣ በጃዊ ቦፌ፣ ፍላ ኦዳና እና ሃያ ጋሻ ቀበሌዎች የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ 'ኦነግ ሸኔ') ታጣቂዎች በሲቪል ሰዎች ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ በፈጸሚቸውና በየጊዜው እየጨመሩ የመጡ ጥቃቶች ምክንያት ከቦራ ወረዳ 919 አባወራዎች/ቤተሰቦች፣ እንዲሁም ከዱግዳ ወረዳ 270 አባወራዎች/ቤተሰቦች ተፈናቅለዋል፡፡
37. መስከረም 17 ቀን 2016 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን ለአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል ፕሮጀክት ሥራ በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩ 6 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሠራተኞች፤ እንዲሁም ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ወረዳ፣ አለም ጤና ከተማ አካባቢ 11 የኢትዮጵያ ግብርና ምርመር ኢንስትቲዩት ሠራተኞች ከቢሾፍቱ ከተማ ወደ አለም ጤና ከተማ ሲጓዙ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") ታጣቂዎች ታግተው ከተወሰዱ በኋላ ከታጣቂ ቡድኑ አባላት ጋር በተደረገ ድርድር ሊለቀቁ ችለዋል፡፡
38. ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ ቦሰት ወረዳ፣ ዶኒ ከተማ የንግድ ሥራቸውን አከናውነው ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ የነበሩ 2 ነጋዴዎች፣ ሹፌርና ረዳትን ጨምሮ በድምሩ 4 ሰዎች በአርሲ ዞን፣ መርቲ ወረዳ፣ አይፋ ዳገት በተባለ ስፍራ ታግተው ተወስደዋል፡፡
39. ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (ኦነግ ሸኔ) ታጣቂዎች የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ ሰደን ሶዶ ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን፣ የወረዳው ዐቃቤ ሕግን፣ እንዲሁም ሌሎች 3 የሕግ ባለሙያዎችን ወደ ቶሌ ከተማ እየሄዱ ሳለ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በማስወረድ ያገቷቸው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም. 2 ዐቃብያነ ሕግ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረዳ በመጓዝ ላይ እያሉ በያያ ጉለሌ ወረዳ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በማስወረድ ካገቷቸው በኋላ በተደረገ ድርድር የተለቀቁ መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል፡፡

## መደምደሚያ

40. ኢሰመኮ ባከናወነው ምርመራ ከመስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል በተለይም በቄለም ወለጋ፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በሰሜን ሸዋ እና በምሥራቅ ሸዋ ዞኖች የተለያዩ አካባቢዎች በሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ "ኦነግ ሸኔ") እና በኢ-መደበኛ የአማራ ታጣቂዎች መካከል በመካሄድ ላይ በሚገኘው ግጭት በርካታ ሲቪል ሰዎች "ለታጣቂዎች እና ለመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ድጋፍ ታደርጋላችሁ፣ ቤተሰቦቻችሁ የእነዚሁ ኃይሎች አባል ናቸው" በሚሉ ምክንያቶች ከሕግ ውጪ መገደላቸውን፣ ለከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት መዳረጋቸውን፣ መታገታቸውን እና ዘረፋ የተፈጸመባቸው መሆኑን ከተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ ነዋሪዎች፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ባሰባሰባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች አረጋግጧል፡፡ እነዚህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት፣ ግጭቶቹ በተከሰቱባቸው አካባቢዎች ላይ ሆን ተብሎ እና በተስፋፋ ሁኔታ በሲቪል ሰዎች ላይ የተፈጸሙ በመሆናቸው፤ እጅግ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት (grave violation of human rights) ተብለው ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡

41. የዚህ ምርመራ ሪፖርት አጠቃላይ ግኝቶች እንደሚያመላክቱት በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም አካላት፣ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሲቪል ሰዎች ላይ ሆን ተብሎ እና በተስፋፋ ሁኔታ ከሕግ ውጪ ግድያዎችን፣ የአካል ጉዳቶችን፣ ዘረፋዎችን እንዲሁም እገታዎችን ፈጽመዋል፡፡ እነዚህ ጥሰቶች ዓለም አቀፍ ባልሆነ ጦርነት አውድ ውስጥ ሲቪል ሰዎችን ተጠቂ ወይም ኢላማ እንዳይሆኑ የመጠበቅ ግዴታን በመጣስ የተፈጸሙ በመሆናቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ፣ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ፣ በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ ማዕቀፍ እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ የተቀመጡ ክልከላዎችን የሚጥሱ እና የጦር ወንጀሎችን እንዲሁም በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ስለሚሆን የተሟላ የወንጀል ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
42. መንግሥት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊነት ሕግጋት ላይ የሚፈጸሙ በዚህ ሪፖርት የተዘረዘሩ ከፍ ያሉ ጥሰቶችን የመመርመር እና አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህን የመሰሉ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የሚደረግ ምርመራም ውጤታማ እንዲሆን ገለልተኛነቱን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ፈጣን፣ እና የተሟላ፣ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት ለተጎጂዎች የተሟላ መፍትሔ ለማስገኘት ጥረት የማድረግ እና ለደረሱ ጉዳቶች ካሳ መገኘቱን የማረጋገጥ እንዲሁም ጥሰቶቹ ዳግም እንዳይከሰቱ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ የመውሰድ ግዴታም አለበት፡፡

# ምክረ ሐሳቦች

**በግጭቱ ተሳታፊ ለሆኑ ሁሉም አካላት፦**

1. ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተኩስ አቁም በማድረግ ለግጭቱ ሰላማዊ መፍትሔ ለማፈላለግ በቁርጠኝነት እንዲሠሩ፤
2. በማናቸውም የግጭት ሂደት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰትን ከመፈጸም እንዲቆጠቡ፣ በግጭቱ የሚፈጸም ጥሰትን በይፋ እንዲያወግዙ እና ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ፤ እንዲሁም
3. በሚቆጣጠሯቸው አካባቢዎች ሰብአዊ መብቶችን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ፤ በሲቪል ሰዎች ሕይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጥቃት ከማድረስ እንዲቆጠቡ፡፡

**ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት**

4. በክልሉ በመካሄድ ላይ በሚገኘው የጦርነት/የትጥቅ ግጭት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰት የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ኃላፊዎችን እና አባላትን እንዲሁም የታጣቂ ቡድኖች አባሎች ተጠያቂ ለማድረግ ነጻ፣ ግልጽ እና የሰብአዊ መብቶች ደረጃን የሚያሟላ የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደት እንዲጀመር፤ እንዲሁም
5. በግጭቱ በሰው ሕይወት፣ በአካል፣ በሥነ-ልቦና እና በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት በማጣራት ተጎጂዎች እንዲካሱ እና መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲደረግ፡፡